# ጥናት አንድ ናሆም 1፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አብዛኛዎቹ የእግዚአብሄር ነብያት መልዕክታቸው የሚያተኩረው በእስራኤል ወይም ደግሞ በይሁዳ ላይ እንደሆነ ይታወቃል፤ ሆኖም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደምንመለከተው የነብዩ ናሆም ትንቢት ትኩረት ያደረገው በዚያን ዘመን ታላቅና በአካባቢው መንግሥታት መሃል የተፈራች በነበረችው በአሶር ዋና ከተማ በሆነችው በነነዌ ላይ ነው። ይህች ከተማ ምናልባትም ከመቶ አመታት በፊት እንደዚሁ ሃጥያቷ በዝቶ እግዚአብሄር ከቸርነቱ ብዛት የተነሳ የንስሃ እድል ለመስጠት ነብዩን ዮናስን በመላክ የንስሃ መልዕክት እንዲያስተላልፍለት ለመላክ እንደወሰነና ዮናስ በእንቢተኛነቱ በተለያዩ ነገሮች ውስጥ አልፎ በመጨረሻ ሄዶ መልዕክቱን በማስተላለፍ ሕዝቡ ንስሃ በመግባት ከፍርድ እንዳመለጠ በትንቢተ ዮናስ ውስጥ እናነባለን።
2. ባል ለሚስቱ ካለው ፍቅር የተነሳ እንደሚቀና፤ ስለ እግዚአብሄር ቀናተኛነት መናገሩ እርሱ ለምርጦቹ ያለውን የፍቅር ስሜት ለመግለጽ እንደሆነ፤ ይህም ማለት ከፍቅሩ የተነሳ እኛ ራሳችንን ለሌላ መስጠታችን ከሚያመጣብን ክፉ ነገር ከመከላከል አንጻር እንጂ እርሱ እኛን ከማጣት የተነሳ ከሚጎድልበት ነገር አንጻር እንደሆነ እረዳለሁ። ምናልባትም ይህንን ሃሳብ በጥሩ መንገድ ሊያስረዳን ይችላል ብዬ የማምነው የጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በ2ኛ ቆሮ 11፡2 ላይ እነርሱን ለክርስቶስ ሙሽራ አድርጎ ለማቅረብ ካለው ፍላጎት የተነሳ እንደሚቀናላቸው የሚናገረው ነገር ሁኔታውን ግልጽ ያደርግልናል እላለሁ።
3. ነብዩ በዝርዝር ያሰፈረልን የእግዚአብሄር ችሎታ፣ ታላቅነቱ፣ መዓትና ቁጣውን ሁሉ በምንመለከትበት ጊዜ፤ የእግዚአብሄር ልጆች ለሆኑት ሁሉ ታላቅ መጽናናት የሚሆንበት መንገድ፤ እንደዚህ ያለ ሁሉን ማድረግ የሚችልና፣ እጅግ ታላቅ የሆነ አምላክ ከእኔ ጎን ካለልኝ ምንም የሚያስፈራኝና ሊያስደነግጠኝ የሚችል ሃይል ሊኖር አይችልም የሚለው ሃሳብ ትልቅ መጽናኛ ይሆናል። በአንጻሩ ደግሞ በእግዚአብሄር ላይ በዓመጽ የሚኖርና በጠላትነት ለሚመላለሰው ሰው፤ እግዚአብሄር የዚህ አይነት ሃይል ያለው መሆኑና ተፈጥሮን ሁሉ የመቆጣጠር ማለትም በወጀብና በአውሎ ነፋስ ውስጥ እንኳን መንገድ ያለው ከሆነ ማምለጫ ሥፍራ ሊኖረው እንደማይችል በማወቅ ከመጽናናት ይልቅ ፍርሃት እንደሚሞላው ግልጽ ነው።
4. በቁ7-8 ላይ ከምንመለከተው፤ የነነዌን ከተማ ጸሐፊው የእግዚአብሄር መልካምነት እንደምታይ ሳይሆን የእግዚአብሄር ጠላት በመሆን እንደምትመላለስ አድርጎ ነው ሲናገር የምናገኘው። የሰቆቃወ ኤርሚያስ ጸሐፊ ልክ እንደ ነብዩ ናሆም በእግዚአብሄር መልካምነት የተስማማ ሲሆን፤ ይህ መጽሐፍ ግን ግልጽ አድርጎ የሚነግረን ተጨማሪ ሃሳብ ቢኖር፤ እግዚአብሄር መልካምነቱ አንደኛ እርሱን ተስፋ ለሚያደርጉት ሰዎች እንደሆነ፤ ሌላው ደግሞ እግዚአብሄርን ለሚፈልጉት ሰዎች እንደሆነ ነው የሚናገረን፤ ይህንኑ ሃሳብ በናሆም ቁ7 ላይም እናገኘዋለን።
5. የነነዌ ሕዝብ ከሓጥያታቸው እንዲመለሱ እግዚአብሄር ዮናስን ከላከበት ጊዜ አንስቶ እስከዚህ ዳግመኛ ናሆምን በሃጥያታቸው እንደሚቀጡ እንዲናገር እስከላከው ጊዜ ድረስ ለእኔ የሚታዩን የእግዚአብሄር ባህርያት፡ ዮናስን ንስሃ እንዲገቡ በመላኩና ከዮናስ ጋራ በመሟገቱ ምህረቱንና ርህራሄውን አያለሁ፤ ፍርድን በናሆም በኩል እንደሚመጣ ከመናገሩ በፊት ቢያንስ ለአንድ መቶ ዓመታት ሳይቀጣቸው በመቆየቱ ደግሞ የትዕግሥቱን ብዛት አያለሁ፤ በመጨረሻም ቁ3 ላይ "እግዚአብሄር በደለኛውን ሳይቀጣ አያልፍም" ብሎ እንደተናገረው፤ ያለውን ነገር በነነዌ ላይ መፈጸሙ በሃጥያት ላይ የሚፈርድ ጻድቅ ፈራጅ እንደሆነም ማየት ችያለሁ።
6. በዘካ 2፡8 ላይ "…የሚነካችሁ የዓይኑን ብሌን ይነካል።" በማለት እንደተነገረው ሁሉ የእግዚአብሄር የሆነውን ሕዝቡን የሚነካበት ማንኛውም ጠላት በእግዚአብሄር ዘንድ የሚታየው ልክ እርሱን ራሱን እንደነካ አድርጎ የሚቆጥር በመሆኑ፤ ለዚህ ነው በዚህ ሥፍራ በናሆ 1፡11-12 ላይ የነነዌ በይሁዳ ላይ ማሴር ልክ በእግዚአብሄር በራሱ ላይ እንደማሴር ሆኖ የተነገረው። አዎን መጽሐፍ ቅዱስ በሰፊው የእግዚአብሄርን አፍቃሪነት፤ እንዲያውም እግዚአብሄር ራሱ ፍቅር እንደሆነ ይናገራል፤ ሆኖም የናሆም ትንቢት የእግዚአብሄርን ሌላ ገጽታ፤ ማለትም እግዚአብሄር ፍቅር ብቻ ሳይሆን በሃጥያት ላይ የሚፈርድ አምላክ እንደሆነም ያሳየናል።
7. እግዚአብሄር ለሕዝቡ ጠላቱን ከጣለለትና በሰላም ተደላድለው እንዲቀመጡ ሁኔታውን አመቻቸላቸው ማለት ምንም ዓይነት ሃላፊነትና ግዴታ ሳይኖርባቸው ይኖራሉ ማለት እንዳልሆነ ቁ15 ላይ የምናነበው ሃሳብ ይጠቁመናል "ይሁዳ ሆይ በዓላትህን አክብር፤ ስዕለትህንም ፈጽም" በማለት ኑሮው እግዚአብሄር አምላኩን በማምለክ ዙሪያ ማተኮር እንደሚኖርበት ይጠቁመናል።
8. መከራና ጭንቀት በበዛበት ሕይወት ውስጥ ሲያልፉ፤ አብዛኛውን ጊዜ ለብዙ አማኞች አዕምሮ ሰይጣን ጥያቄ ሆኖ እንዲሰማቸው በጆሯቸው ሹክ የሚልላቸው ጥያቄ "ታዲያ እግዚአብሄር መልካም አምላክ ከሆነና፤ ይወደኛል ብለህ የምታስበውን ያህል ቢወድህ፤ ለምን ይህ ሁሉ ሁኔታ በአንተ ላይ ደረሰ?" በማለት የእግዚአብሄርን መልካምነት ከጥያቄ ውስጥ እንድናስገባው ግብግብ ማቅረብ ልማዱ ስለሆነ፤ ይህንን ተንኮሉን ተገንዝቦ ጆሮን ለእርሱ አለመስጠት ጥበብ ነው።

# <u>ጥናት ሁለት ናሆም 2፡1-3፡19 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ነነዌ እግዚአብሄር ሊያመጣባት ካለው ነገር ለማምለጥ ይህንን ዓይነት ዝግጅት እንድታደርግ በነብዩ ናሆም በኩል ሲነግራት እውነትም እነዚህ ነገሮች ማምለጫ ሊሆኗት እንደሚችሉ ለመናገር ሳይሆን፤ በማፌዝና በማላገጥ ምሽግን በመጠበቅ፣ ወገብን በመታጠቅና ያላትን ሃይል ሁሉ ለማሰባሰብ መሞከር ምንም ፋይዳ ሊኖረው እንደማይችል ለመናገር እንደሆነ ነው የማምነው። በቁ1 ላይ እግዚአብሄር ለየት ባለ መንገድ ከእርሱ ዘንድ ሊመጣ ያለውን ቅጣት ለማስወገድ ነነዌ ማድረግ የምትችለው ነገር እንደሌለ የተናገረ ሲሆን፤ በቁ2 ላይ ደግሞ ከዚያው ሃሳብ ጋራ በተገናኘ፤ ያሳለፉት ብዙ ነገሮች ቢኖሩም እንኳን የያዕቆብ ክብር መመለሱ እርግጠኛ እንደሆነ በመናገር የቀደመውን ሃሳቡን ዳግመኛ ያረጋግጣል።
2. ምንም እንኳን እነዚህ ቁጥሮች ሁሉ ስለ ነነዌ መውደቅ አይቀሬነት ገልጠው የሚናገሩ ይሁን እንጂ፤ በተለይም ቁ6ት ላይ "የወንዙ በር ወለል ብሎ ተከፈተ፤ ቤተ መንግሥቱም ወደቀ" በማለት ገና እንደሚሆን ነገር አድርጎ ከመናገር ባሻገር በከተማይቱ ላይ ዛሬውኑ ሆኖ እንደሚያየው ነገር አድርጎ ነው ናሆም ሁኔታውን የሚያቀርበው። የአሶር የጦር ሰራዊት በአካባቢው ሁሉ የታወቀና ማናቸውንም ሃይል እየደመሰሰ እዚህ እንደደረሰ ቢታወቅም እንኳን፤ በዚህን ወቅት የተነሳበት እግዚአብሄር ራሱ እንጂ የምድር ጦር ሰራዊት ስላልሆነ፤ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ለመዋጋት ቢወጣም እንኳን ተሰነካክሎ እንደወደቀና ምንም ማድረግ እንዳልቻለ ነው የምንመለከተው።
3. ነነዌ ላይ ዛሬውኑ እንደደረሰባት አድርጎ በቁ10 ላይ ከሚናገራቸው ሰባት ነገሮች መሃል የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ የሚከተሉት ናቸው፡ ተበዝብዛለች፣ ተዘርፋለችና፣ ተራቁታለች (እነዚህ በንብረት ላይ ያተኮሩ ናቸው)፤ እንደ ሰው አድርጎ የተናገራቸው አራቱ ነገሮች ደግሞ፡ ልብ ቀልጧል፣ ጉልበት ተብረክርኳል፣ ሰውነት ተንቀጥቅጧልና፣ ፊት ሁሉ ገርጥቷል የሚሉት ናቸው። አሶር አስፈሪነቱ በመንግሥታት ሁሉ ዘንድ እንደታወቀ ሁሉ፤ በዚህ ክፍልም የተመሰለበት የአራዊት አለቃ ተብሎ በሚታወቀው በአንበሳ እንደሆነ እንመለከታለን።
4. እንደሚታወቀው የአሶር መንግሥት በዚያን ዘመን በብርቱ  የታወቀለት፣ ሁሉንም ያንበረከከ መንግሥት ነበረ፤ ሆኖም በ612 ዓ.ዓ ባቢሎናውያን፣ ከለዳዊያንና የሜዶ ፐርሺያ መንግሥታት በታላቅ አመታት ስለመቱት መውደቁን እናውቃለን። በ2፡13 ላይ ነብዩ ናሆም ሊነግረን የሚፈልገው ነገር ቢኖር፤ ምንም እንኳን እነዚህ መንግሥታት ጣሉት ይባል እንጂ መንግሥታቱ በእግዚአብሄር እጅ የመጠቀሚያ መሳሪያዎች መሆናቸውን ነው የምናየው። ሰረገላቸውን እንደሚያቃጥልና እንደሚያጤስ፣ ደቦል አንበሶቻቸውን (ብርቱ ሰዎቻቸውን) ሰይፍ እንደሚበላ፣ የሚበሉትን ነገር እንደሚያጡና ከእንግዲህ ወዲህ የመልዕክተኞቻቸው ድምጽ እንደማይሰማ ይሆናሉ።
5. በዚህ በናሆ 3፡1 ላይ ይህች እግዚአብሄር ለፍርድ እያዘጋጃት ያለችዋን የነነዌን ከተማ ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ሃሳቦች፡ የመጀመሪያው የደም ከተማ ይላታል፣ በማስከተል ደግሞ ዘረፋ የሞላባት ከተማ እንደሆነች ሲናገር፣ ቀጥሎ ደግሞ ብዝበዛዋ ወይም ምርኮዋ ከብዛቱ የተነሳ ተግዞ እንደማያልቅ ይነግረናል። ምንም እንኳን ፍርዱ ገና ያልሆነና ሁኔታዎቹም ገና ያልተፈጸሙ ቢሆኑም እንኳን፤ ነብዩ ናሆም እንደሆነና እንዳለቀለት አድርጎ የሚናገርበት ምክንያት እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ፤ እግዚአብሄር አምላክ አንድን ነገር ተናገረ ወይም ቃል አወጣ ማለት ከተከናወነ ነገር ምንም ተለይቶ ስለማይታይ ይመስለኛል ይህንን አነጋገር የተጠቀመው።
6. በቁ4-7 ውስጥ ያሉትን እነዚህን ሁሉ ሃሳቦች በአንድ ቃል ብቻ አጠቅልል ብባል ብዙ አማራጭ ቃላቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ብረዳም እንኳን አብዛኛዎቹ ከውርደት ጋራ የተዛመዱ ቃላት ናቸው ብዬ ስለማምን "አዋርድሻለሁ" በሚለው ቃል አካትታቸዋለሁ። ነነዌ ይህ ሊሆንብኝና ሊደርስብኝ አይችልም በማለት ራሷን እንዳታታልል እግዚአብሄር የተጠቀመበት መንገድ ከዚህ ቀደም ተብላ የማትገመተውና ነገር ግን የተዋረደችውን ከተማ ኖእ አሞንን በምሳሌነት እንድታይ ያሳስባታል።
7. ጭፍሮችህ ሁሉ ሴቶች ናቸው የሚለው አነጋገር፤ በአሶር ሰራዊት ውስጥ ወንድ የሚባል አንድም ወታደር የለም ሁሉም ሴቶች ብቻ ናቸው ለማለት ሳይሆን፣ በዚህን ሰዓት እግዚአብሄር ድንጋጤን በሰራዊቱ ላይ ስለሚልክ ሁሉም ፈሪዎች ሆነዋል ለማለት ነው።
8. በዘመኑ በታላቅነቷ የታወቀችውና ማንም ከነበረችበት የከፍታ ሥፍራ ያወርዳታል ተብሎ የማትገመተዋን የአሶር ዋና ከተማ የሆነችውን ነነዌን እግዚአብሄር ከብዙ ትዕግሥት በኋላ የደረሰችበትን እንኳን ማወቅ እስከማይቻልበት ድረስ ካዋረደ፤ በእኛም ሕይወት በአካባቢያችን የምናየውንና የምንሰማውን ክፉ እኛ በምናስበው መንገድና ጊዜ ባይሆንም እንኳን፤ እግዚአብሄር ግን በራሱ ሰዓትና በራሱ ጊዜ ልክ እንደ ነነዌ ታላቅና የማይገረሰስ በመሰለበት ሰዓት ሊያዋርደው እንደሚችል ማስታወስ ያስፈልገናል።